# ማን ይፈራል ሞት?

ያ ፈሪ፣ ቦኾርቧዣ፣ ኣይመጣ ፊት-ለፊት
ሁሌ ተደብቆ፣ ተጋርዶ በወንፊት…
ዘልዓለም ኣድፍጦ ሲመጣ ድንገት
ኣንቆ በጉረሮ፣ ዘልሎ ወደ ኣንገት!

ወንድ በሆነና ፊት ለፊት በመጣ
ኣወርድበት ነበር የፈጣሪን ቁጣ!
ምነው ጀግና ሆኖ ቢመጣ ብቻውን
ኣሳየው ነበረ ኣቶ ሞት ፍዳውን!

ፈሪ፣ ፍርፋሪ፣ ምድጃ ቆፋሪ
ዘላለም ታጅቦ በብዙ ኣጫፋሪ
ስቃይና፣ ሕመም፣ ችጋርን ኣክሎ
ከተፍ ይላል እንጂ ጥርሶቹን ኣሹሎ!

ብቻውን ቢመጣ ኣንዱን ሳያስከትል
ወግቼ፣ ቀድጄ፣ ኣንጀቱ እስኪቆስል
ድራሹን ኣጥፍቼው፣ እግረ-እጀ ቆራጣ
ኣደርገው ነበረ ዳግመኛ እንዳይመጣ!

ኣድፍጦ መምጣቱ፣ ኣስከትሎ ኣሽከር
ጉረሮየን ኣንቆ ኣልወጣበት ቀምበር!
የኣዳም ዕዳ ሆኖ ጭራሹን የማይቀር…
ብቻውን ቢመጣ መች እለቀው ነበር?

እስከዚያው ልደሰት፣ የቻልኩትን ልሥራ
ልጨፍር፣ ልቆፍር፣ ላርምና፣ ልዝራ
ኣጉል መጨነቁ ለማይቀረው ዕዳ
ሞት በሚመጣ ዕለት ያበጠው ይፈንዳ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።

